★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 34 ቁጥር 7 ግንቦት 2001 ዓ.ም.

# ትግላችን ለብዙሃኑ፡ ትግላችን ለኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስንል የሀገሪቷ ዕድገትና ህልውና መሠረት የሆኑት አርሶ አደሩ ላብ አደሩ፥ ሴቶች፥ ወጣት ተማሪዎች፥ አስተማሪዎች፥ የቢሮ ሠራተኞች፥ ነጋዴዎች ምዕመናን፥ ሠርቶ አደሮች ታክሲ ነጂዎች፥ የሕዝብ ማመላለሻ ሰራተኞች፥ ጭቁን ወታደሮች፥...ወዘተ ለመጥቀስ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙሃኑን የማይጠቅም የብዙሀኑን መብት የማያስከበር ሥርዓት ከንቱ ነው፡፡ በመሆኑም ነው ሕዝብን ያላቀፈ ትግል መና ይቀራል ብቻ ሳይሆን ከሕዝብ የተነጠለ ድርጅትም ሆነ ትግል ከውሀ እንደወጣ አሳ ይቆጠራል፤ ይሞታል የሚባለው፡፡ ይህንንም በተለያዩ ጊዜያት ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ የገለጸው መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡ ታዲያ የሕዝቡ ትግል መና እንዳይቀር፤ ሕዝቡን የፖለቲካ ሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ ደግሞ ሁሌም ለወቅቱ ተስማሚ የሆኑ የትግል መፈክር በማውጣት መቀስቀስ፤ ማደራጀት፥ ማንቃትና በቀጣይነት ማታገልን የግድ ይላል፡፡ የፖለቲካ ትግል በመሠረቱ ያለፈውን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አዛምዶ በመመርመር፤ በሱም ተመርኩዞ ወደፊት ሊሆን የሚችለውን አማትሮ ለማየት ጥረት ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ይህም በመሆኑ፥ ያሳለፍንበትን በርካታ ውጣ ውረዶችን የሚያስታውሰን ብቻ ሳይሆን እንደፖለቲካ ድርጅት ሆነ እንደሕዝብም ታሪካዊ በዓላትን ያከበርንበትን ወርሃ ግንቦት በመነሻነት በመጠቀም፤ በተለይ የአርሶ አደሩንና የላብ አደሩን ሁኔታ እንደገና ጠለቅ አድርጎ መመርመርና ማጤን አግባብነት ያለው ይሆናል የሚል ጽኑ እምነት አለን፡፡

ከዚህ አንጻር በጣም የሩቁን ትተን በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን አርሶ አደሩ በምን ሁኔታ ላይ ነበር? አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሳ ግንዛቤ የሚሹ ለመሆናቸው አጠያያቂ አይደለም፡፡ የአፄው ዘመን አርሶ አደር በአብዛኛው ከባርነት ባላነሰ ሁኔታ ለረዥም ዘመን ኖሯል፡፡ በወቅቱ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው የእርስት የመሬት ስሪት ምክንያት አብዛኛው የሰሜኑ አርሶ አደር ከገባርነት ያመለጠ ቢሆንም በደቡቡ፥ በመሃል አገር፥ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ የነበረው ግን በጭሰኝነት (በገባር) የመሬት ስሪት ሲሰቃይ የቆየ ነበር፡፡ መጠኑ ዝቅ ያለ ይሁን እንጂ የጭሰኝነት የመሬት ስሪት በሰሜኑም የሀገራችን ክፍሎች የነበረ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የጣሊያን ወራሪ ኃይል በአርበኞቻችን ተጋድሎ ተሸንፎ ከሀገራችን ከወጣ በኋላ በነበሩት 33

ዓመታት ማለትም እስከ 1966 ድረስ መሬት በግል የመያዝ ሕግና ደንብ ወጥቶ ተግባራዊ ቢሆንም መሬቱን የተቀማውና ገባር የተደረገው አርሶ አደር የዚህ ተጠቃሚ አልነበረም። በሰሜኑና በማህል አገር እርስቱን ለማስከበር ወይም በባለ ሥልጣን የተነጠቀበትን መሬት ለማስመለስ በየፍርድ ቤቱ እየተንገላታ ጉዳዩም ለልጅ ልጅ እየተላለፈ ፍትሕ ሳያገኝ ቀይቷል። በደቡቡ፥ በመሃል አገር፥ በደቡቡ ምሥራቅና በደቡብ ምዕራቡ ክፍል ግን የእርሻው መሬት በመሬቱ ላይ ካለው አርሶ አደር ጋር ለአዲሱ ባለቤት ይሸጥ ወይም ይሰጥ ስለነበር አርሶ አደሩ ከባርነት ያለተለየ ጭሰኛ መሆን እንጂ የማይደፈር የመሬት ባለቤትነት መብት አልነበረውም። አርሶ አደሩ በሽያጭም ሆነ በስጦታ ለአዲሱ ጌታው ከተሸጠ በኋላም ልክ እንደ ድሮው ማረሱን ይቀጥላል፤ የምርቱን ሲሶ፥ እርቦ፥ ወይም እኩሉን በፍትህ ብሄሩ ህግ በሰፈረው መሰረት ለመሬቱ ባለቤት ይሰጣል፤ ግብር ይከፍላል፤ ቢያንስ የምርቱን ሲሶ በአስራት መልክ ለቤተ ክህነት ይከፍላል። የአርሶ አደሩ በደል በዚህ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። መኳንንቶች ግብር/ግብዣ፥ ሠርግ ባረጉ ቁጥር ሰንጋውን ሙክቱን፥ ማሩን ቅቤውን፥ ጤፉን የወጥ እህሉን፥ ...ወዘተ (በጥንት ዘመን እንደነበረው ሁሉ) እንዲያቀርብ ያረጉት ነበር። በአንዳንድ አካባቢዎችማ እሱ የማይጠቀምበትን መሬት (መሬታቸውን) እንዲያርስና እንዲዘራ፤ እንዲያርምና እንዲያጭድ ብሎም ከጎተራቸው እንዲከት ያዙት ነበር። በዚህ ዓይነት የሚበዘበዘው አርሶ አደር የተሟላ ምግብ አግኝቶ፤ ወግ ያለው ልብስ ቀይሮ፤ ለእግሩ ጫማ ሸምቶ፤ ከቁር ሆነ ከሀሩር የሚከላከልበት ወግ ያለው ቤት ሠርቶ፤...ወዘተ የሚኖርበት ሁኔታ ውስጥ አልነበረም። በጎተራውም እስከሚቀጥለው ሰብል መግቢያ የሚያደርሰው በቂ ምርት የሌለው አርሶ አደር ቁጥሩ በሚሊዮኖች ነው የነበረው።

በሌላ በኩል መንግሥት ነኝ የሚለው ክፍል አርሶ አደሩ ለብዙ ዓመታት ሲጠቀምበት የቆየውን ኋላቀር የእርሻ ዘዴ ለማሻሻል እርምጃ ባለመውሰዱ፥ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ክሊኒኮች፥ ለልጆቹ ትምህርት ቤቶች፥ ምርቱን ወደ ገበያ የሚያደርስበት መንገዶች ስላልተሠሩለትና ንጹህ የመጠጥ ውሃ፥ (የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ትተን)...ወዘተ፥...ወዘተ፥ የሚያገኝበት መንገድም ስላልተምቻቸ አርሶ አደሩ እድሜውን የገፋው በድህነት ነበር። በየአካባቢው ያሉ የመንግሥት መዋቅሮች የጭቆናውን ሕግ በአርሶ አደሩ ላይ ለመጫን የተሰየሙ እንጂ ለአርሶ አደሩ አገልግሎት ለመስጠት የተደራጁ አልነበሩም። በአንጻሩ በሃብት በሥልጣኑ የተመካ ሁሉ እንደፈለገው ለማንገላታት የሚጠቀምባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች፥ ፍርድ ቤቶች፥ ወረዳ/አውራጃ አስተዳዳሪዎች፥ የቤተ ክህነት ኃላፊዎች ...ይዋቀሩለታል። ከሁሉም በላይ "ስዩመ እግዚአብሔር" የሆነው ንጉሥ የማይነካና የማይከሰስ በመሆኑ በሱ የሚታዘዘውንና የሚታወጅበትን ሁሉ ያለምንም ጥያቄና ማወላወል መፈጸም ነበረበት። በርህብ እየረገፈም ንጉሡ የልደት በዓላቸውን ዲል ባለ ሁኔታና በፈንጠዝያ ማክበራቸውን ሊያግደው፥ ምንም ሊያረገው አይችልም ነበር። እንግዲህ ከመነሻው ላይ እንደተጠቀሰው ይህን አርሶ አደር ከባርነት ባልተናነሰ ደረጃ ይኖር ነበር ስንል ለማጋነን ሳይሆን ከነዚህ ዕውነቶች ተነስተን ነው።

ለመሆኑ የላብአደሩስ ሁኔታ በዚሁ ዘመን ምን ይመስል ነበር?

ምንም እንኳን ከጣሊያን ወረራ በፊት አንዳንድ እንዱስትሪዎች ቢኖሩም ይህን ያህል የሚባሉ አልነበሩም:: ከጣሊያን መውጣት በኋላም ከባድ ኢዱስትሪዎች ሳይሆኑ ቀላል የጨርቃ ጨርቅ፥ የጫማ፥ የቆዳ፥ የለስላሳና የአልኮል መጠጥ፥ የምግብ ነክ ማምረቻዎች፥ የሲሚንቶ፥ እንዲሁም የመንገድና የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ፥ የስኳር ማምረቻ፥...ወዘተ መሰል ኢንዱስትሪዎች ነበር የተቋቋሙት:: በነዚህ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከሥራቸው ጋር ባልተመጣጠነ ለረጅም ሰዓታት የሚሰሩ ላብ አደሮች ነበሩ:: ዘመናዊ እርሻ በሀገር ደረጃ ያን ያህል የሰፋ ይዞታ የነበረው አልነበረም:: ሆኖም ወንጂ፥ መተሃራ፥ ተንዳሆ፥ አብደራፊ-መተማ፥ ሰቲት ሁመራ፥...ወዘተን የመሰሉ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የቀን፥ የምርት ወቅትና ቋሚ ሠራተኞችን የሚያስተናግዱ ነበሩ:: እንዲሁም እንደከፋና የሲዳሞ ያሉ የቡና እርሻዎች ቀላል የማይባሉ የምርት ወቅት ላብ አደሮች ነበሯቸው:: ከነዚሁ ጋር የተያያዙ የቡና አጣሪና አበጣሪ ኩባንያዎች እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ክፍያ የሚሰሩ በተለይ የሴቶች ላብ አደሮችን ያቀፉ ኩባንያዎችም ነበሩ:: ከዘመናዊነት ማደግ ጋር በተፈጠሩ የአገልግሎት መሥሪያ ቤቶች ውስጥም የተሰማራው ሠራተኛ ቁጥሩ የሚናቅ አልነበረም - የሰው ማመላለሻ አውቶቡስና የዕቃ ማጓጓዣ ጭነት ማመላለሻ ኩባንያዎች፥ የምድር ባቡር ኩባንያ፥ በትምህርትና በጤና መስክ የተሰማሩና በልዩ ልዩ ሌሎች የአገልግሎት መሥሪያ ቤቶች የነበሩት ሰራተኞች ሁሉ እዚህ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው::

እነዚህ በልዩ ልዩ ኢንዱስትሪዎችና ዘመናዊ እርሻዎች፤ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የሚሰሩ ላብ አደሮች/ሠራተኞች ቀደም ሲል ለብዙ ዓመታት የሥራ ሰዓታቸው፥ የሳምንት እረፍታቸው፥ የጡረታ መብታቸው፥ የህመም እረፍታቸው፥ በሥራ ላይ ለሚደርስባቸው የአካል ጉዳት ዋስትና እንዲሁም ለሴቶች የወሊድ እረፍት ባይተዋር ነበሩ:: እነዚህን በዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማህበር ሕግ መሰረት ይከበርላቸው ዘንድ ለመጠየቅ ምንም አቅም አልነበራቸውም:: ክፍያቸው ሕይወታቸውን በሚያቆይ ደረጃ ብቻ ነው የነበረው:: ያችኑ እንዳላጣ በሚል በተለይ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት ላብ አደሮች ከሳምንት እስከ ሳምንት ያለምንም እረፍትና ከ12 - 14 ሰዓታት በሚደርስ ይሰሩ ነበር:: ከዓመት እስከዓመት ኑሯቸው ፈቅ ሳይል ሳይሻሻል፤ ቤተሰቦቻቸውን በበቂ አብልቶ ማሳደር እየተሳናቸው፤ ልጆቻቸውም በትምህርት መግፋት ሳይሆን ፈጥነው ለቤተሰብ ኑሮ መደጎሚያ ለማግኘት ሥራ መሰማራት ነበር እጣቸው:: ይህን ሁኔታቸውን ለመቀየር ቢያንስ የተባበረ አቅም ለማግኘትና ትግላቸውንም በተደራጀና በተቀነባበረ መልክ ለማካሄድ የሚያስችላቸውን ማኅበር ለመመሥረት እጅግ ከባድ ትግል አድርገዋል፤ መስዋዕትነትንም (እነ አበራ ገሙን ያስታውሷል) ከፍለዋል:: ባደረጉት ትግል፤ ምንም እንኳን በአንድ ወጥ ሁሉም ዘንድ የተስተካከለና የተሟላ ነው ባይባልም፤ ቢያንስ የሥራ ሰዓታቸውን፥ የሳምንትና የዓመት እረፍታቸውን፥ የጡረታ መብታቸውን፥...ወዘተ ለማስከበር ችለው ነበር:: በየተቋሞቻቸው በማኅበር መደራጀት መቻላቸው አልፎም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያስተሳስራቸው

አንድ ማኅበር (ኢ.ሰ.አ.ማ -ን) መመስረታቸው በራሱ አንድ የትግላቸውና የመስዋዕትነታቸው ውጤት መሆኑን ታሪክ የመዘገበው ነው::

በዚህ ወቅት ንጉሡ ፍጹም ሥልጣን ስለነበራቸውና ሥርዓቱም ይህንኑ ንጉሣዊ አገዛዝ የሚያስከብርና የሚያስጠብቅ በመሆኑ ለሰፊው ሕዝብ መብትና የኑሮ እድገት ማሰብና ለተግባራዊነቱ ሥልጣኑን ጥያቄ ውስጥ ማስገባትና ለመንቀሳቀስ መሞከር የሚያስቀጣ፥ የሚያሳስር የሚያስገድልም ወንጀል ነበረ:: በመሆኑም፥ ምንም እንኳን ላብአደሩ መስዋዕትነትን ከፍሎ ማኅበሩን ለመመሥረት ቢችልም፥ አገዛዙም ሆነ የአገዛዙ ደጋፊ ባዕድ ሀገር ባደረጉት አሻጥርና ተፅዕኖ ላባደሩ በልዩ ልዩ ጊዜና ዘርፍ የተለያዩ መብቶቹን ለማስከበር ባደረገው ትግል ያገኘው ውጤት ውሱን ነበር:: ስለዚህም ኑሮው ብዙም ሳይሻሻል፣ ፍትህን ሳያገኝ፣ በበሽታ እየተጠቃ፣ በድህነት እየተቆራመደ፣ ካለ እድሜው እየረገፈ በደልን መሸከም ተገደደ :: በነዚህ ሁለት የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የደረሰው ይህ ነው የማይባል ድህነትና በርሃብ መርገፍ፣ ቅጥ ያጣ ፈላጭ ቆራጭነት፣ የሕዝቡ ፍጹም መብት አልባነት ለብዙ-ብዙ ዘመናት ተንሰራፍቶ በመኖሩና ብሶቱም ሞልቶ በመፍሰሱ፣ ሕዝብ እምቢኝ፥ በቃኝ ብሎ ባካሄደው አብዮት 'እሽ!' አትበሉኝ ባዩ የአፄው ሥርዓት ተገረሰሰ፣ አከተመ::

ያንን ተከትሎ የሕዝብን ትግል አደናቅፎ በመጣው የደርግ አገዛዝ ዘመን የአርሶ አደሩም ሆነ የላብአደሩ ሁኔታ በተጠበቀውና በሚፈለገው ደረጃ ሊሻላል አለመቻሉ የቅርብ ጊዜ ትዝታና ሀቅ ነው:: ለውጥ ካልን ዘንዳ ፊውዳላዊው የአፄው ሥርዓት በሕዝቡ አብዮት ተገርስሶ ከነግሳንግሱ አክትሟል:: ይህ በራሱ ሥዩመ እግዚአብሔር የተባለውም ቢሆን በሕዝብ አመጽ ከሥልጣን ሊወረወር እንደሚችል፣ ለስንት ሺህ ዘመን ሀገሪቷን በማን ይነካኛል እብሪት ጨምዶ የያዘው አፄያዊ ሥርዓት በሕዝብ ትግል ማብቃቱ ለሕዝቡ የማይናቅ የራሱን ትምህርት ሰጥቶ አልፏል:: አርሶ አደሩ በእርግጥም ከሌሎች ለውጥ ፈላጊ ሀገር ወዳድ የህብረተሰቡ ክፍሎች ጋር በመሆን “መሬት ለአራሹ“ በሚለው መፈክር ሥር ባደረገው ጠንካራ ትግል፣ እርቦ፥ አሥራት፥...ክፈለኝ፣ አጥሬን እጠርልኝ፣ ለልጄ ሠርግ ቅቤ፥ ጤፍ ጫንልኝ የሚለውን አስቀርቷል:: ምንም እንኳን በትግሉ የጭሰኝነት ሥርዓቱን እንዲያከትም ቢያረግም፣ እንዲሆን በታገለለት ዴሞክራሲያዊ የሕዝቡ ሥርዓት ባለመተካቱ፣ ወታደራዊው ደርግ የራሱን የአምባገነን ሥርዓት በቦታው በመሰየም ነበር ሁኔታው የቀጠለው:: በሠራተኛው መንግሥት ስም እራሱን የሰየመ ወታደራዊ ፍጹም አምባገነን ሥርዓት ስለነበር፣ መሬት ሆነ ቤት፥ በሀገሪቱ ያሉ ትላልቅ ይሁኑ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች፥ ኩባንያዎች ሳይቀሩ በቁጥጥሩ (በአገዛዙ ቁጥጥር) ሥር አድርጎ ነው ደርግ/ኢሰፓ ዘመኑን የጨረሰው:: ይህም በኢትዮጵያ አርሶ አደሩ የሚታረሰው መሬት ከንጉሣዊውና መሳፍንቱ ቁጥጥር ወጥቶ (በርስትነት ያለው ሳይቀር) እንዳለ በወታደራዊው አስተዳደር ሥር ገብቶ ነበር ማለት ነው:: ስለዚህም አሁንም በደርግ ዘመን “መሬት ለአራሹ“ በታገሉለትና ከፍተኛ መስዋዕትነት በከፈሉለት የማህበረሰብ ክፍሎች ፍላጎት ተግባራዊ አልሆነም - መሬት የአገዛዙ፣ በጨቋኞች ቁጥጥር ሥር ነበርና!

አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ አዛዥ ናዛዥ የሚሆንበት፣ መብቱን የሚያስከብርበት ማኅበር ማቋቋም አይችልም ነበር፡፡ ዴሞክራሲና ደርግ ባላንጣዎች በመሆናቸው ፍላጎቱንና ምኞቱን በነፃ የሚገልጽበት ሁኔታ አልነበረውም፡፡ ባንፃሩ በግድ ለፖለቲካ ቁጥጥሩ በሚያመቸው መልክ (ነፃነት በሌላቸው) በገበሬና ልዩ ልዩ ስም የተለጠፈባቸው የህብረት እርሻ በሚባሉ ማኅበራት እንዲደራጅ ተደርጎ፥ ተቀፍዶ ነው የተበዘበዘው፡፡ በነዚህ የደርግ አስተዳደር መሣሪያ በሆኑ ማኅበራት አማካይነት የስንግ እየተያዘ፥ ለጦርነት ሲጋዝ፣ ለጦርነት ያለውን አሚጦ ሲያዋጣም የደርግ ዘመንን አሳልፏል፡፡ ከብቱን፥ ጥሪቱን ብቻ ሳይሆን ልጁንም ገብሯል፡፡ ስንቱ ገበሬና የገበሬ ልጅ እንደረገፈ ቤቱ ይቁጠረው ከማለት ሌላ፣ ደርግ ምንም የኑሮ መሻሻል ሆነ የመንፈስ እርካታ ሳይሰጠው ነው ወደ መቃብሩ የወረደው፡፡ በደርግ ሶሻሊዝም ተብዬ ለስሙ መሬት ለገበሬው ተሰጠ ይባል እንጂ አርሶ በሚያመርተው እራሱን እንኳን አጥግቦ የሚያድርበት ሁኔታ ባለመኖሩ፥ ለተደጋጋሚ የጦርነት ዘመቻ ጥሪ ከሕይወቱ እስከጥሪቱ በመገበሩ፣ በከፍተኛ ረሀብ በተደጋጋሚ ተቆልቷል፥ ረግፏል፡፡ ይህንንም የዓለም ሕዝብ ሳይቀር ያወቀው የመዘገበው ጉዳይ ነው - የ1976/1977 ሚሊዮኖች የረገፉበትን ረሀብ ያስታውሷል፡፡ ባጭሩ በደርግም ዘመን አርሶ አደሩ በሚያርሰው መሬት ላይ የኔ የሚለው (የመሸጥ፥ የመለወጥ) መብትና በነፃ ተደራጅቶ መብቱን የሚያስከብርበት ምንም ዓይነት ማኅበር አልነበረውም፣ ማቋቋምም አይችልም ነበር፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠረው የሀገራችን ገበሬ በልቶ ጠግቦ ማደርን፥ ንጹህ የመጠጥ ውሃና የህክምና አግልግሎትን፥ ለልጆቹ ት/ቤትን፥ ከሌላ ወገኑ ጋር የሚያገናኘው መንገድና ትራንስፖርትን፥ በአጠቃላይም መብቱን፥ ...ወዘተ እየተመኘ ሳያገኝ ቀርቶ ሲሰቃይ መባጀቱም ሊካድ የማይችል ሀቅ ነው፡፡

በመንግሥቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ ዘመን የላብአደሩ ሁኔታም ከአርሶ አደሩ የተለየ አልነበረም፡፡ እንዲያውም ደርግ በሠራተኛው ስም የሚጠራ ፓርቲን (ኢሠፓ-ን) አቋቁሞ ሲያላግጥበት ከረመ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ "አሁን የሠርቶ አደሩ ፓርቲ ስለተቋቋመ ሠራተኛው በሀቀኛው መሪያችን ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም መሪነት ድሉን ተቀዳጅቷል" የሚል ዘፈን ነበር ጠዋት ማታ የሚቀነቀንለት፡፡ ስለዚህም፥ ነፃ ማኅበር፥ ለመብት መታገል፣ የራሱን መሪዎች በነፃ መምረጥ፣ ...ወዘተ መጠየቅ ቀርቶ ማሰብም አይፈቀድለትም ነበር፡፡ የሙያ ማኅብሩን ተቀምቷል፣ መሪዎቹም (በግፍ የተገደሉትን እነ ማርቆስ ሀጎስና ሌሎቹንም ያስታውሷል) አጥቷል፡፡ በየሚሰራበት ኢንዱስትሪ ሆነ ተቋም ወይም የመንግሥት እርሻ፥ ምን እንደሚናገር ሳይሆን የት እንደሚውል፥ ከማን ጋር እንደሚውል ጭምር የካድሬ ዘብ ቆሞለት ፍዳውን ሲያይ ቆይቷል፡፡ ልክ እንደ አርሶ አደሩ ለጦርነት ተማግዷል፣ ጉልበቱንና ሃብቱን ብሎም ልጁን ሳይቀር ገብሯል፡፡ ኑሮው አሽቆለቆለ እንጂ አላደገም፡፡ መብቱ የበለጠ ተረገጠ እንጂ አልተሻሻለም፡፡ የቀይ ሽብርና የአፈና ሰለባም ሆኖ አልቋል፡፡

ዛሬ ወዳለንበት የወያኔ የመከራ አገዛዝ ስንመጣ የአርሶ አደሩም ሆነ የላብ አደሩ ሁኔታ አሁንም እንደቀደሙት ሁሉ ከመጥበሻው ወደ እሳቱ መሆኑ አልቀረለትም:: ቀደም በደርግ መንግሥት በግዳጅ የእርሻ ማኀበር መፍጠሩ ቀርቶለታል:: ለላብአደሩም በስሙ (ለመግዛት) በደርግ የተመሰረተለት ኢሠፓ አክትሟል:: ለሕዝብ ሁሉ በቦታው በወያኔ ሕገ መንግሥት ተብየው የተደነገገ የኀሳ አጥር ተበጅቷል:: በተግባርም የኢትዮጵያ ላብአደሮች በሀገር አቀፍ ደረጃ እራሳቸውን አዋቅረው ኢሰማኮን አደራጅተው የሰራተኛውን ጥቅም ለማስከበር ያደረጉትን ሙከራ፤ መሪዎቹን በማዋከብ፥ በመወንጀልና በማሰር ብሎም አገር ጥለው እንዲሰደዱ በማረግ፤ የድርጅቱንም ንብረት በመዝረፍ በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ - የጠባብ አገዛዙ ሥርዓትና አደረጃጀትን ተቀብሎ ሠራተኛውን በዚያ ሀዲድ ላይ ብቻ እንዲጓዝ ሌት ተቀን የሚሰራ ቡችላ (ተለጣፊ) ድርጅት/ማኀበር ተብዬ አቋቁሟል:: ደርግ ያለመሸፋፈን በኢትዮጵያ ምድር እሱ እስካለ ከራሱ ፖለቲካ ውጭ የሚያራምዱትን የፖለቲካም ሆነ የሕዝብ ድርጅቶችን እንደማያስተናግድ ግልፅ አድርጎ እንደነበረ ሲታወስ ወያኔ ግን ሕገ መንግሥቴ ነው በሚለው ሳይቀርና በይፋም በሚሰጠው ዲስኩር፤ በነፃ የመደራጀትን ዴሞክራሲያዊ መብት በሀገሪቱ መኖር ጠዋት ማታ እየለፈፈ በተጨባጭ ግን አምባገነናዊነቱን መቀጠሉ በሕዝብ የታወቀና የተጋለጠ ነው:: የወያኔ ዴሞክራሲ ቀፎና ባዶ መሆኑን በተጨባጭ ለስንት ቀናት በፀሐይና በዝናብ፥ በሙቀትና በቁር፥ በረሀብ ጭምር ለመብታቸው በመስቀል አደባባይ ሲቆሉ ከርመው ያለምንም ውጤት ተበትነው የቀሩትን ላብአደሮች/ሠራተኞች እንደምሳሌ ያስታውሷል:: የወያኔ አስተዳደር የሚያደርስባቸውን በደል ለማስረዳት ከጎጃም የአካባቢውን አርሶ አደር ወክለው አዲስ አበባ የመጡትም ምን ዓይነት ፍዳ እንዳዩና ጉዳያቸውም መልስ ሳያገኝ መደምደሙንም ልብ ይሏል:: ሀገሪቱን፥ ብሎም ኩባንያዎችንና እንዱስትሪዎችን ሙሉ ለሙሉ በፖለቲካው ሥር አድርጎ የሚያስተዳድረው ወያኔ፤ የላብ አደሩን ደሞዝ ዝቅተኝነቱን እንኳን ትተን ለስንት ወራት ደሞዝ ሳይከፈለው በችግር እንደሚቆላ በቅርብ የድሬደዋ የምድር ባቡር ሠራተኞች በግልፅ አደባባይ ያወጡት ጉዳይ ነው:: ይህ ደግሞ የዋጋ ንረት በስንት እጥፍ አድጎ ባለበት ሁኔታ መሆኑንም ያስተውሏል:: የወያኔ አገዛዝ በመዋቅር ማስተካከያ ስም በዘጋቸው፤ በሸጣቸው (ገልብጦ እራሱ በገዛቸው) ፋብሪካዎችና ኩባንያዎች ውስጥ ይሰሩ የነበሩትን ላብአደሮች/ሰራተኞች በርካታዎቹን ያለምንም ዋስታና ሜዳ ላይ ጥሏቸዋል፤ የተቀሩትንም ለጠባብ ፖለቲካው መጠቀሚያ በማድረግ በውዧቸዋል ወይም ተክቷቸዋል:: አሁን በዚህ ወቅት ሥራን ለመቆጣጠርና ለማሳደግ በሚል ሽፋን "መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ" የሚል አዲስ ሕግ አውጥቶ ለሱ ታማኝ ያልሆኑትን ሠራተኞች እየመነጠረ ነው::

በሀገራችን ያለው የኑሮ ውድነት ይህ ነው ተብሎ መነገር ከሚያስቸግርበት ደረጃ ደርሷል:: የስራ አጡ ቁጥር እየጨመረ ነው:: የላባደሩ ክፍያ ካለው የዕቃና የአገልግሎት ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እድገቱ አፍን ሞልቶ ወደታች/ወደ ቁልቁል ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ ላይ ለአገዛዝ ፖለቲካው

የማይመቹትን በየጊዜው ግምገማ እያለ ይመነጥራል። አርሶ አደሩማ ሁሌም በገሌ እንደሚለው ነው። ወያኔ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ ከግንቦት 1983 ዓ.ም. ጀምሮ ስንት ሕዝብ በረሃብ እንደረገፈ፣ ዛሬም ስንት ሚሊዮኑ በእርዳታ እንደሚኖር በዓለም አቀፍ የምግብ ድርጅት ሳይቀር ጠዋት ማታ የሚሰማ እሮሮ እንደሆነ አለ። የደርግ ተቃዋሚ ሆኖ በምንቀሳቀስበት ወቅት ያነገበው ሀፍረ ተቢስነቱና ለሕዝብ ግድየለሽነት ጠባዩ አገርሽቶበት የሀገሪቱን ሕዝብ አጥግቦ ማሳደር የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ግዴታ ይመስል፣ የወያኔ አገዛዝ "14 ሚሊዮን ሕዝብ ለረሃብ ተጋልጧልና በጊዜ እርዳታውን ካላደረሳችሁ ለሚደርሰው የሕዝብ መርገፍ ተጠያቂ አይደለሁም፣ እነሆ በጊዜ እንድታቀርቡ ነግሬያለሁ፣ ዋ!" ሲልም አድምጠናል። እነመለስ አዲስ አበባን ተቆጣጥረው እራሳቸውን በሥልጣኑ መንበር ባስቀመጡ ሰሞን "በቀን ሦስት ጊዜ እናበላዋለን" ብለው እንዳልተመጻደቁ ሁሉ፣ ዛሬ እንዲህ ያለ ዓይን ያወጣ ልመና ሲያካሂዱ አለማፈራቸው ነው የሚያስገርመው፣ የሚያስደምመውም። አርሶ አድሩና ላብ አደሩ በትንሹ ከዛሬ 40 ዓመት በፊት የት ነበሩ አሁንስ ምን ላይ ናቸው? የአገዛዞቹ መቀያየር መሰረታዊ ለውጥን አስከትሎላቸዋል ወይስ አዲስ ንጉሥ አንጂ ለውጥ መቼ መጣ የተባለውን በቅንነት ለመቀበል እንገደዳለን ስንል መልሱ ግልፅ ነው። የወያኔ አገዛዝ ፀረ ሕዝብ ፀረ ዴሞክራሲ ሆኖ ይገኛል። ትላንት የለውጥ ትግልን የወለደው አስከፊ ሁኔታ ዛሬም አለ--ይባስ ብሎ የሀገር ህልውና ራሱ በአደጋ ላይ ወድቋል።

መሠረታዊ ነገሮችን አስቀምጠን እናጠቃል። በምንም ዓይነት መልኩ ብናየው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ዋና ኃይል የሆኑትን አርሶ አደሩንና ላብአደሩን፦

- የሥልጣን ምንጭ፥ የሥልጣን ባለቤት ያደረገ ሥርዓት በሌለበት፣
- ያለምንም የመንግሥት ተጽዕኖ በነፃ መደራጀት በማይችሉበት፣
- በሀገራቸው ፖለቲካዊ፥ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ (የራሳቸው) ሕይወት ውስጥ በተግባር (ያለምንም ተጽዕኖ) በማይሳተፉበት
- የሚተዳደሩበትን ሕገ-መንግሥት በመቅረጽና ይሁንታን ሰጥተው ባላቆሙት ሥርዓት በሚገዙበት/በሚተዳደሩበት
- በገዛ ሀገራቸው ኬላ ሳይበጅባቸው በነፃ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፥ ከሰሜን እስከ ደቡብ እንደልባቸው መንቀሳቀስ፣ ሠርተው፥ ነግደው ሸምተው መኖር በማይችሉበት
- ... ወዘተ

ሁኔታ ይህ አገዛዝ የአስተዳደር ለውጥን አምጥቷል ብሎ መናገር በሕዝብ ላይ መቀለድ ነው። ዛሬም በወያኔ ነፃነትና ዴሞክራሲ እንደተነፈጉ ናቸው፣ የተሰየመባቸው እንጂ በትክክለኛና በነፃ ምርጫ ያስቀመጡት መንግሥትም የላቸውም። በሀገራቸው በየትኛውም ቦታ ያለምንም ተጽዕኖ እንደልባቸው የሚኖርበት ሁኔታ የለም። በተገኘው መልካም አጋጣሚና በልዩ ልዩ የትግል ሁኔታዎች ሁሉ በመጠቀም ድምፃቸውን ቢያሰሙም፣ ምርጫቸውን ቢገልፁም ድምፅ ተቀምተው ተፈጁ ታሰሩ እንጂ ያተረፉት ለውጥ ከቶም የለም።

ለዚህም ነው፥ የወያኔ/ኢሕአዴግ አምባገነን ሥርዓት አክትሞ ለየካቲት አብዮት ጭምር መንስዔ የሆኑት ችግሮች ይወገዱ፣ የሕዝብ ፍላጎቶችም ይሟሉ ዘንድ ትግሉን በተቀናጀ መልክ ከማጧጧፍ ሌላ መፍትሄ የለም። አርሶ አደሩና ላብአደሩ በተቀናጀ መልክ ትግሉን እንዲገፉ አቅም አግኝተው ለውጤት እንዲበቁ ባመቸው መንገድ ሁሉ እንዲደራጁ መጣር ተገቢ ነው። የወያኔ ዘመን እንዳለፉት ሁለት ሥርዓቶች ሁሉ በሕዝቡ በተባበረ ትግል የሚወድቅ ነው። በመሆኑም በአርሶ አደሩና ላብአደሩ ውስጥ የሚካሄደው የቅስቀሳና ድርጅታዊ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ይህ ሲሆን ነው ደግሞ እውነተኛው የሕዝብ ክንድ አበረ፣ የሕዝብ ጉልበት ፈረጠመ ማለት የሚቻለው። በሀገራችን 80 ከመቶ የሚሆነው ይህ የህብረተሰብ ክፍል በሁሉም መስክ የለውጡ ዋና ጉልበት ሁኖም መካተት ይኖርበታል። የዚህን ጣምራ ኃይል ጥቅምና ፍላጎት ያላካተተ ለውጥ መሰረታዊ ለውጥ ነው ለማለት ከቶ አይቻልም። ኢሕአፓ ከመነሻውም፥ የዛሬ 37 ዓመት በፊት ያስቀመጠው ይህ - አርሶ አደሩንና ላባደሩን-- ማለትም ብዙሃኑን ሠርቶ አድር -- የሥልጣን ምንጭና የሥልጣን ባለቤት የማድረግ ዓላማ ዛሬም ዓላማው ነው! ለዚህም የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዛሬም በቆራጥነት መታገሉን ቀጥሏል።

የብዙሃኑ የሥልጣን ባለቤትነት በትግላችን እውን ይሆናል!